# ቅኔን ማን ይቀውኘው?

አብርሃም በየነ

ሁለቱ ፀጋዬዎች
ሞክሼ ገ/ መድህኖች
አንደኛው- ሎሬት ጀቢራ
ሌላኛው - ታጋይ ደብተራ።

ሎሬቱ - በተውኔት ጮራ
ደብተራው - በትግሉ ጎራ
የቁአጠሩትን - የቅኔ ቱማታ
ስንታገል - ልንፈታ
የደብተራው -ደብዛው ጠፋን ተዘርፎ
የሎሬቱን አገኘነው - በመቃ በዕሩ ገዝፎ።

## የጉድ አገር

የአፈጣጠራችን - ነገር
ሰው እንዲለን - የጉድ አገር
ሁለቱም - ለትግል
አፈጣጠራቸው - ለየቅል።

አሲምባዎች - በግፈኛ ንጉሥ የሕዝብ አበሳ
ደደቢቶች - ለሸዐቢያ እገዛ በሙሴ ባራኪ ቅስቀሳ።

አሲምባዎች - ለሀገር
ደደቢቶች - ለመንደር።

አግኣዚና አረጋዊ - ቢኒያምና ወዲ ደበሳይ
ገዳይና - ተገዳይ
ሁለቱም - ከትግራይ።

አሲምባዎች - በዕኩልነት አንድነትን ለማንገስ
በጋራ የወል ጎጆ መቀለስ
ደደቢቶች - ጎጠንነትን በመለያየት ለማጎልመስ
በመገንጠል የወል ጎጆን ማፈራረስ።

አሲምባ - የጨለማ መቅረዝ
ደደቢት - የሀገር መርዝ።
ጎጆወን - በመቀለስ
እና
ጎጆወን - በማፍረስ
ደደቢትና - አሲምባ
ምን ጊዜም - ሆድና ጀርባ።

## የስንዴ ገመና

አያደርጉት ነገር - ጡብኛ ወይ ቂጣ
አይጋግሩት ህብስት - ከምጣድ አይወጣ
ምጣዱ እስኪሰማ - የሚነድ ጠፍቶ
ሊጥ ሞላው አገሩን - ተቦክቶ ተቦክቶ።